## “እንድና እንድን እስር” የማድረግ ተልእኳችንን እንወጣለን!

# ድንጋይና ቅዝምዝም የሚወረወረው ጣፋጭ ፍሬ ያፈራ ዛፍ ላይ ሰለሆነ የሊቀ መንበራችን መታገት አያስበረግገንም!

(አብዱራህማን አህመዲን፤ ከሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ - በግል)
ahayder2000@gmail.com

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ ሰሞኑን በዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃን ሰፊ ሽፋን የተሰጠው የሳዑዲ ዓረቢያ መንግስት “የፀረ-ሙስና ዘመቻ” ነው። አንዳንዶቻችሁ “ታዲያ በሳዑዲ ዓረቢያ ጉዳይ ምን አገባህና ነው ብዕር ያነሳኸው?” የሚል ጥያቄ ታነሱ ይሆናል። በርግጥ ከዜግነት አኳያ የሳዑዲ ዓረቢያ መንግስት ጉዳይ አይመለከተኝም፤ አያገባኝም። ለዓመታት አፎቱ ውስጥ ከትቼው የነበረውን መንጎለ-ብዕር ጥቀርሻውን አራግፌ በሳዑዲ ዓረቢያ ጉዳይ ላይ እንዳነሳ ግድ ያለኝ ግን ነገሩ ወዲህ ነው።

እኔ ብቻ ሳልሆን በርካታ ኢትዮጵያውያን ሳዑዲ ዓረቢያን አስመልክቶ ሃሳብ እንድንሰጥ ግድ የሚሉን በርካታ ጉዳዮች አሉ። በዋናነት ከአምስት መቶ ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጎቻችን በሳዑዲ ዓረቢያ ምድር መኖራቸው የሳዑዲ ዓረቢያን መንግስት ለመክሰስም ለመውቀስም እንድንነሳ ግድ ይለናል። እኔንም በብእሬ “ላሌ ጉማ”ን እንዳቀነቅን ያደረገኝ፤ “እንድ” ግን ደግሞ “እንደ ሺ የሚቆጠር” የኢትዮጵያ “ልጅ” በሳዑዲ ዓረቢያ መንግስት “ታገተ” መባሉን ሰምቼ ነው። ይህም “የአንድ ሺ” የሆነ “የኢትዮጵያ ልጅ” ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ይባላሉ። ከአናቱ እስከ እግር ጥፍሩ በሙስና እንደነተበ ዓለም የሚያውቀው የሳዑዲ ዓረቢያ መንግስት የእኛውን ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲንን በሙስና የመወንጀል የሞራል ልዕልና የሌለው መሆኑ ነው ንዴቴን ያባሰው።

ወደ ጽሑፌ ዋና ፍሬ ነገር ከመግባቴ በፊት ለአንባቢዎቼ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ሁለት ማሳሰቢያዎችን ማስቀደም ወደድሁ። የመጀመሪያው ማሳሰቢያዬ፤ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የማሰፍረው ሃሳብ የእኔ የግል አስተያየት እንጂ ከምሰራበት መስሪያ ቤት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው መሆኑ ይታወቅልኝ የሚል ነው። ሁለተኛው ማሳሰቢያዬ ደግሞ፤ ይህንን ጽሁፍ ያሰናዳሁት ሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ውስጥ ስለምሰራ (የሼህ ሙሐመድ ተቀጣሪ ስለሆንኩ) ሳይሆን፣ ሰሞኑን በማህበራዊ ሜዲያ አማካይነት ስለ ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ የሚናፈሰው አሉባልታ ትክክል ስላልሆነ ትንሽም ብትሆን የማውቃትን ሀቅ በመናገር ከሊቀ መንበራች ጎን እንድቆም ህሊናዬ ስለጎተጎተኝ ነው።

የጽሑፌን ይዘት በተመለከተ፤ በቅድሚያ ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ በኢትዮጵያ ያላቸውን ኢንቨስትመንት አጀማመርና ተዛማጅ ጉዳዮችን በአጭሩ አነሳለሁ። በመቀጠል ስለ ሼህ ሙሐመድ በኢንተርኔትና በማህበራዊ ሜዲያዎች ተደጋግመው የሚነሱ አሉባልታና ጭፍን ወቀሳዎችን እያጣቀስኩ አቀርባለሁ። የፖለቲካ ሣይንስና የኢኮኖሚክስ ባለሙያ እንደመሆኔ ሰሞኑን የሳዑዲ ዓረቢያ መንግስት ሼህ ሙሐመድ አል-አሙዲንን ያገተበትን ምክንያት በተመለከተ አንዳንድ ነጥቦችን ለማንሳት እሞክራለሁ።

እንደሚታወቀው ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት የጀመሩት ከደርግ ውድቀት በኋላ ነው። “ሚድሮክ ኢትዮጵያ” የተባለው ኩባንያ ከመቋቋሙ በፊት ሼህ ሙሐመድ ከአቶ ታደለ ይድነቃቸው ተሰማ ጋር “አል-ታድ” የሚል ኩባንያ አቋቁመው በኮንስትራክሽን ዘርፍ ነበር የተሰማሩት። ሸራተን ሆቴል የተገነባውም በዚሁ በ“አል-ታድ” ይመስለኛል።

ከዚያ በኋላ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ተቋቁሞ በደርግ መንግስት ይዞታ ስር የነበሩ የልማት ድርጅቶችን መሸጥ ሲጀምር ሼህ ሙሐመድ አክሳሪና ሊዘጉ የተቃረቡ ተቋማትን በመግዛት

በርካታ ኢትዮጵያውያንን ከስራ አጥነትና ከበረንዳ አዳሪነት አድነዋል። ተጨማሪ አዳዲስ ኩባንያዎችንም በማቋቋም ኢንቨስትመንታቸውን አስፋፍተዋል። የሥራ እድል ፈጥረዋል።

ከኢንቨስትመንቱ በተጨማሪ በበጎ አድራጎት ስራቸው የሚታወቁት ሼህ ሙሐመድ በአሁኑ ወቅት በመላ ሀገሪቱ 75 ኩባንያዎች አሏቸው። እነዚህም ኩባንያዎች በኮንስትራክሽን፣ በሆቴል፣ በፋይናንስና አገልግሎት፣ በእርሻና በመሳሰሉት የሥራ መስኮች የተሰማሩ ናቸው። በእነዚህ ኩባንያዎችም በአጠቃላይ እስከ 100 ሺህ የሚደርሱ ቋሚ፣ ጊዜአዊና የኮንትራት ቅጥር ሠራተኞች የሥራ እድል አግኝተዋል ተብሎ ይገመታል። ይህም የሰው ኃይል ሼህ ሙሐመድን ከመንግስት ቀጥሎ ብዙ የሥራ እድል የፈጠሩ ባለሃብት ያደርጋቸዋል።

በኢትዮጵያ በሚያደርጉት የንግድና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በርካታ ኢትዮጵያውን የንግድ ሸሪኮችን በማፍራትም ይታወቃሉ ሼህ ሙሐመድ። ከዚህ በተጨማሪ፤ ሼህ ሙሐመድ በተለያዩ ሀገራት ያካበቱትን የንግድ ድርጅት የአሰራርና የአስተዳደር ስልት ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት በርካታ የሰው ኃብት ልማትና የቴክኖሎጂ ሽግግርም አድርገዋል።

ከላይ እንደተገለጸው በኢትዮጵያ ያሉት የሼህ ሙሐመድ ኩባንያዎች ብዛት 75 ገደማ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ሃያ አምስቱ ኩባንያዎች “ሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ” በሚል ጃንጥላ (Umbrella) ስር የተደራጁና በእውቁ መሐንዲስ በዶ/ር ኢንጅኔር አረጋ ይርዳው CEO/ፕሬዝዳንትነት የሚመሩ ናቸው። የዚህ ጽሁፍ አቅራቢም በቴክኖሎጂ ግሩፑ ውስጥ ከኦፊሰርነት ተነስቶ በአሁኑ ወቅት በማናጀርነት በማገልገል ላይ ይገኛል።

ወደ ሚድሮክ ከመምጣቴ በፊትም ሆነ አሁን ድረስ ሚድሮክን በተመለከተ በርካታ አሉባልታዎች ሲናፈሱ ሰምቻለሁ። ከአራት ዓመታት በላይ በድርጅቱ ውስጥ በነበረኝ ቆይታ በየጥጋ ጥጉ ሲራገቡ የነበሩት አሉባልታዎች ሁሉ መሰረተ ቢስ መሆናቸውን በቅርብ ርቀት የተመለከትኩ በመሆኑ አንዳንዶቹን እያነሳሁ መሰረተ-ቢስነታቸውን ለማመላከት እሞክራለሁ።

የዛሬ 17 ዓመት ገደማ ጀምረው ሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕን በማቋቋም በCEO/ፕሬዝዳንትነት እየመሩ ያሉት ዶ/ር ኢንጅኔር አረጋ ይርዳው ናቸው። ዶ/ር ኢንጅኔር አረጋ ይርዳው ይህንን ኃላፊነት ሲረከቡ በቴክኖሎጂ ግሩፑ ውስጥ የነበሩት 5 ደካማ ኩባንያዎች ብቻ ነበሩ። ከአምስቱ ውስጥ የተሻለ ሕይወት አለው ሊባል የሚችለው ሚድሮክ ጎልድ ኃ. የተ. የግል ኩባንያ ብቻ ነበር። እሱም ቢሆን በ35 ፈረንጆች “የተወረረ” እና ከገቢው ወጪው የሚያመዝን ኩባንያ ነበር።

ዛሬ በቴክኖሎጂ ግሩፑ ስር ያሉት ኩባንያዎች ብዛት 25 ደርሷል። እንደ ትረስት፣ ኩዊንስ ማርኬት፣ አውቶ ሜይንቴናንስ፣... ወዘተ. የመሳሰሉት ኩባንያዎች ዶ/ር ኢንጅኔር አረጋ ራሳቸው “ሀ” ብለው ያቋቋሟቸው ናቸው። አንዳንዶቹ ለምሣሌ፤ ኢትዮ-ድሪም፣ ጂቱ እና አንሊሚትድ ፓኬጂንግ፣... የመሳሰሉት ደግሞ በአሰራር ድክመት ከስረው ሊዘጉ ሲያጣጥሩ ሼህ ሙሐመድ ለዶ/ር አረጋ እየሰጧቸው የአሰራር ስርዓታቸው እንዲሻሻልና እንዲያገግሙ የተደረጉ ናቸው። ይህንን ሁሉ ለማንሳት የተገደድኩት በመቀጠል የማነሳቸውን አሉባልታዎች በጥልቀት ለማየት እንዲረዳኝ በማሰብ ነው።

አሉባልታ ከሼህ ሙሐመድ ተለይቶ አያውቅም። ገና ወደ ኢትዮጵያ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ የአሉባልታ ዝናብ ይዘንባል። የሀሜት ጎርፍ ይጎርፋል። የበሬ ወለደ ጅረት ይፈሳል። ሼህ ሙሐመድ ሼራተን ሆቴልን መገንባት እንደጀመሩ “ሰውየው ይህንን መሬት የወሰዱት ምኒልክ ቤተ-መንግስት አጠገብ ጣሊያን ቀብሮት የሄደውን ማርትሬዛ ብር በዘዴ ቆፍረው ለመውሰድ ነው...” ተብሎ መወራቱን አስታውሳለሁ። ሼህ ሙሐመድ ራሳቸው ይቆፍሩት ይመስል እንዲህ ያለ አሉባልታ መፈብረክ ትርጉም የለውም። የሆነ ሆኖ በቁፋሮው ሂደት እንኳን የማርትሬዛ ብር የኃይለ ስላሴን ምስል የያዘ ሣንቲም ስለመገኘቱ አላህ ይወቅ! በሼህ ሙሐመድ በኩል ግን ሸራተን በተሰራበት አካባቢ ለነበሩ 500 ገደማ ተነሺዎች ወደ ሲኤምሲ በሚወስደው መንገድ በተለምዶ “አል-ታድ ሚካኤል” በሚባለው አካባቢ ቤት ሰርተው በነፃ መስጠታቸው እውነት ነው። እንዲህ ያለውን ቤት ሰርቶ የመስጠት ተግባር እንኳን ኢንቨስተር መንግስትም አድርጎት አያውቅም።

ሌላ መሰረተቢስ አሉባልታ እናንሳ። በቴክኖሎጂ ግሩፑ ስር ካሉ ኩባንያዎች ሼህ ሙሐመድ የሀገሪቱን ሀብት እየበዘበዘ ነው እንዲባሉ ያደረጋቸው ሚድሮክ ጎልድ ነው። ሼህ ሙሐመድ ከፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አንዳንድ ሙትቻ ኩባንያዎችን እየገዙ ስማቸው እየገነነ ሲመጣ አሉባልታውም ተጠናክሮ ቀጠለ። ሚድሮክ ጎልድን እንደገዙ “ሼህ ሙሐመድ የሀገሪቱን ወርቅ እያወጡ ቀጥታ ውጪ ሀገር እየወሰዱ ቸበቸቡት…” የሚል ሀሜት በሰፊው መወራት ጀመረ። እውነታው ግን እንደዚያ አልነበረም። ከአገዛዙ ጀምሮ የነበረውን ሂደት እንመልከት።

ሚድሮክ ጎልድ ለጨረታ ሲቀርብ ከሚድሮክ ሌላ የፈረንሳይና የሌሎች ሀገሮች ተጫራቾች ተሳትፈው ነበር። ሼህ ሙሐመድ በ170 ሚሊዮን ዶላር ገደማ ለመግዛት ባቀረቡት ዋጋ አሸነፉ። የሚገርመው ነገር ሼህ ሙሐመድ ካሸነፉ በኋላ ተጨማሪ 50 ሚሊዮን ዶላር ከፍለው ሚድሮክ ጎልድን በ220 ሚሊዮን ዶላር ገደማ ነበር የገዙት።

በነገራችን ላይ ሼህ ሙሐመድ ሚድሮክ ጎልድን ሙሉ ለሙሉ አይደለም የገዙት። የኢትዮጵያ መንግስትም ባለ ድርሻ ነው። በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያን መንግስት በመወከል የስራውን ሂደት የሚከታተለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው። እናም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሳያውቀው አንዲት ግራም ወርቅ አይሸጥም። የመሸጫ ዋጋውም የሚወሰነው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው።

መንግስት ከወርቅ ሽያጩ የሚገኘውን የትርፍ ድርሻውን (dividend) በሂሳብ ባለሙያ እየተሰላ፣ በኦዲተር እየተረጋገጠ በየዓመቱ ይወስዳል። የትርፍ ግብርም ይሰበስባል። የሮያልቲ ክፍያም ያገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ሼህ ሙሐመድ ከራሳቸው የትርፍ ድርሻ ላይ ለክልሉ መንግስት በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በችሮታ ይሰጣሉ። አሁንም ከዚህ በተጨማሪ ሼህ ሙሐመድ ከራሳቸው ድርሻ ላይ ለአካባቢው ህብረተሰብ ት/ቤት፣ የጤና ተቋማትና ሌሎች የመሰረተ ልማት አውታሮችን ገንብተዋል። መንገድ ሰርተዋል። ይህንን ሀቅ የአካባቢው ህብረተሰብና አባ ገዳዎች ጭምር ጠንቅቀው ያውቁታል። መላው የድርጅቱ ሰራተኛም ያውቀዋል። ሼህ ሙሐመድ እየዘረፉት ነው የሚባለው ሚድሮክ ጎልድ ይህንን የሚመስል አሰራር ያለው መሆኑን እኔም አይቻለሁ።

ሌላው በየኢንተርኔቱና በማህበራዊ ሜዲያ ሼህ ሙሐመድን በተመለከተ ሲናፈስ ያየሁት አሉባልታ “ሼህ ሙሐመድ ሁሉንም የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በርካሽ ዋጋ እንዲገዙ ተመቻችቶላቸዋል…” የሚል ነው። ይህ የወሬ ቱማታ ተራ ስም ማጥፋት መሆኑን ለማሳየት አንዳንድ እውነታዎችን በማስረጃ አስደግፌ ላቅርብ።

ከ1987 እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ ባሉት ጊዜአት ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ 260 የሚሆኑ የቀድሞ መንግስት የልማት ድርጅቶቸን በሽያጭ ለግለሰቦች አስተላልፏል። ከነዚህ ውስጥ ሼህ ሙሐመድ የገዟቸው 23 ብቻ ናቸው። (ቀሪዎቹ 237 ኩባንያዎች ለሌሎች ለውጭ ሀገርና ለኢትዮጵያውያን ባለ ሀብቶች ነው የተሸጡት) በመቶኛ ሲሰላ ሼህ ሙሐመድ የገዟቸው ዘጠኝ በመቶ (9%) ያህሉን ብቻ ነው ማለት ነው። ይህንኑም ከሌሎች ጋር ተጫርተው እየተሸነፉም እያሸነፉም ያገኙት ውጤት ነው። ሼህ ሙሐመድ ከመንግስት “ልዩ ድጋፍ” ቢረግላቸው ኖሮ ቢያንስ ቢያንስ ሃምሳ በመቶ የሚሆኑትን ኩባንያዎች በገዙ ነበር።

እዚህ ላይ “ሼህ ሙሐመድ የገዟቸው ኩባንያዎች የተሻለ ይዞታ ያላቸውንና አትራፊዎቹን ነው” የሚል ተጨማሪ ሹክሹክታም ይነሳል። ይሁን እንጂ ሼህ ሙሐመድ የገዟቸው ኩባንያዎች ከስረው በመዘጋት ሂደት ላይ የነበሩ ወይም ሊዘጉ አንድ ሀሙስ የቀራቸው አሊያም ሊሸጡ ባለመቻላቸው መንግስት መጣያ አጥቶ የተቸገረባቸው ድርጅቶች ናቸው።

ለምሳሌ በዓይኔ ያየሁትን ልንገራችሁ። ሼህ ሙሐመድ ከገዟቸው ውስጥ አንዱ መልጌ ወንዶ የሚገኘው እርሻና የቲማቲም ድልህ ማምረቻ ፋብሪካ ነው። ይህ ፋብሪካ በ1930ዎቹ በጣሊያን ቅኝ ገዢዎች የተቋቋመ፣ መለዋወጫ የማይገኝለት፣ በሞዲፊክ መከራውን ያየ ሙት ፋብሪካ ነው። ያንን ፋብሪካ

ያመረተው ፋብሪካ በምድር ላይ የሚኖር አይመስለኝም። ደሴ ያለው የለስላሳ መጠጥ ፋብሪካም ተመልሶ ካህሳይ በተባሉ ኤርትራዊ በጣሊያን ዘመን የተቋቋመ ባልቴት ፋብሪካ ነው።

ማገናዘብ የሚችል ህሊና ላለው ሰው እነዚህን ሞት አፋፍ ላይ የነበሩና አክሳሪ ስመ ኩባንያዎችን ሼህ ሙሐመድ መግዛታቸው ያስመሰግናቸው እንደሆነ እንጂ ከቶም የሚያስወቅሳቸው ሊሆን አይችልም። እንኳን እጅ መንሻ ሰጥተውና ከባለስልጣት ጋር ተሞዳሙደው ሊገዟቸው በነፃ ቢሰጧቸው ሊቀበሏቸው የማይገባቸው ናቸው።

ሼህ ሙሐመድ እነዚህን ሙት ፋብሪካዎች ከገዟቸው በኋላ በኩባንያዎቹ ላይ አስፈላጊውን ማሻሻያ እንዳያደርጉ መንግስት “የንግድ ዘርፉን መለወጥ አይቻልም” የሚል አስገዳጅ ድንጋጌ በማስቀመጡ ሰውየው ለተጨማሪ ኪሳራ መዳረጋቸውን መገመት ይቻላል። እንደ ዶ/ር ኢንጅኔር አረጋ ያለ ሌት ተቀን እንቅልፍ አጥቶ የሚሰራ ጥበበኛ የንግድ ሥራ መሪ ባይዛቸው ኖሮ ለሼህ ሙሐመድ እንኳን ትርፍ ሊያስገኙ ከስረው ይዘጉ ነበር። ይህ ሁኔታ ደግሞ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞችና ግማሽ ሚሊዮን ያህል ቤተሰባቸውን ጎዳና ላይ እንዲወጡ ያደርግ ነበር።

በአጠቃላይ፤ እነዚህ ሁኔታዎች የሚያሳዩት ሼህ ሙሐመድ አላግባብ ሀብት ማግበስበሳቸውንና በሙስና መዘፈቃቸውን ሳይሆን፣ እንደ ኢትዮጵያዊ ለሀገራቸውና ለወገናቸው የክፉ ቀን ደራሽ መሆናቸውን ነው። እዚህ ላይ አንድ ነገር ግልጽ ማድረግ እወዳለሁ። ይኸውም፤ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሼህ ሙሐመድ በኢትዮጵያ ውስጥ በሙስና የተዘፈቁበት ሁኔታም ሆነ በሙስና ያፈሩት ሀብት የለም አልኩ እንጂ “በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት 75 የሼህ ሙሐመድ ኩባንያዎች ውስጥ ሙስና የሚባል ነገር የለም፣ የሼህ ሙሐመድ ሀብትና ንብረት በነቀዙ ሰራተኞቻቸውና የኩባንያ መሪዎች አልተመዘበሩም ወይም አይመዘበሩም” እያልኩ እንዳልሆነ እንዲታወቅልኝ አደራ እላለሁ።

በኢትዮጵያ ያለውን የሼህ ሙሐመድን የኢንቨስትመንት ሁኔታ ካየን በኋላ ውጪ ወዳለው ሁኔታ ማምራት ተገቢ መሆኑን አምናለሁ። ይሁን እንጂ ሼህ ሙሐመድ በውጪ ሀገራት ያላቸው የንግድ እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል ስለማላውቅ ምንም ነገር ማለት አልችልም። በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል ማንሳት የምፈልገው ሰሞኑን በሼህ ሙሐመድ ላይ በሳዑዲ ዓረቢያ መንግስት የተፈጸመቀውን እገታና የእገታውን ምክንያት በተመለከተ ይሆናል።

ሰሞኑን ሼህ ሙሐመድ የታገቱበትን ምክንያት በተመለከተ በመገናኛ ብዙሃን፣ በኢትዮጵያውያን ማህበራዊ ሜዲያዎችና በህብረተሰቡ ዘንድ ብዙ ብዙ ነገር እየተወራ ነው። የሼህ ሙሐመድ ነገር ይህን ያህል መወያያ የሆነው ሼህ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው እንደ ዜጋ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ካላቸው ወደር የማይገኝለት ሚና በመነሳት ስለሆነ የሚያስገርም ጉዳይ ሆኖ አይታየኝም። ስለሆነም የሼህ ሙሐመድ ጉዳይ መታየት ያለበት ከአንድ ተራ ዜጋ ጉዳይ አንጻር ሳይሆን እኚህ ትልቅ ባለሀብት ካላቸው ጉልህ ሚና አኳያ መሆን ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ።

ቀደም ሲል መግቢያየ ላይ እንደጠቀስኩት በሙያየ ፖለቲካል ኢኮኖሚስት ነኝ። እናም የሼህ ሙሐመድን የእስር ምክንያት ከፖለቲካም ከኢኮኖሚም አኳያ ለመዳሰስ እሞክራለሁ። በዚህ መሰረት ሦስት አመላካች ነጥቦችን ለማንሳት እወዳለሁ። **የመጀመሪያው ነጥብ፤** ሼህ ሙሐመድ የአሜሪካ መንግስት የትኩረት ዒላማ መሆናቸውን በተመለከተ ነው።

ብዙዎቻችን እንደምናውቀው እ.ኤ.አ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ አሜሪካ “አል-አሙዲ የአሸባሪዎች ደጋፊ ሊሆን ይችላል” በሚል ጥርጣሬ በሼህ ሙሐመድ ላይ ክትትል ታደርግ እንደነበር ይነገራል። በተለይም ቦስኒያ ውስጥ በሚንቀሳቀስና ለአል-ቃዒዳ ድጋፍ ያሰባስባል ተብሎ በሚጠረጠር አንድ የእርዳታ ድርጅት ሰነድ ውስጥ ስማቸው ተገኝቷል በሚል ሰበብ በሼህ ሙሐመድ ላይ ክትትል እንደሚደረግ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ይሁን እንጂ፤ ቦስኒያ ውስጥ በሚንቀሳቀሰው የእርዳታ ድርጅት ሰነድ ውስጥ የሼህ ሙሐመድ ብቻ ሳይሆን የሌሎችም ታዋቂ ሰዎችና ባለሃብቶች ስም ተገኝቶ ስለነበርና እነሱም ተጠይቀው ለድርጅቱ እርዳታ መስጠታቸውን አምነው፤ ነገር ግን ድርጅቱ ለአል-ቃዒዳ መስራቱን እንደማያውቁ ገልጸው ስለነበር አሜሪካም በወቅቱ የወሰደቺው እርምጃ አልነበረም። ስውር ክትትሉ ግን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አልተቋረጠም። አሁን ትራምፕ ወደ ስልጣን ሲመጡና የሳዑዲ አዲሶቹ ልዑላን "ሼህ ሙሐመድ ከቀድሞው ንጉስ አብደላ ቤተሰብ ጋር በሽሪክነት ስለሚሰሩ ለአልጋዩ ያሰጋል ወይም አድርግ ያልነውን አያደርግም..." የሚል ስጋት ሲያድርባቸው (ሙስናን ሽፋን አድርገው) ይህቺን ካርድ መዘው እያስፈራሩባት እንደሆነ የመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ።

**ሁለተኛው ነጥብ፤** ሼህ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ቁንጮ ባለ ሀብት በመሆናቸው የታሰሩበት ምክንያት ከህዳሴው ግድብ ጋር ሊያያዝ ይችላል የሚል ነው። እንደሚታወቀው የህዳሴ ግድብ በመሰራቱ የግብፅ መንግስት "ጥቅሜ ይነካል" በሚል መንፈስ ሳይሆን "በምቀኝነት መንፈስ" የግድቡን ሥራ ለማደናቀፍ እንቅልፍ አጥቶ ይዋትታል። አንዴ የኤርትራን መንግስት በመደገፍና በማስተባበር፣ ሌላ ጊዜ በውጪ ሀገራት ያሉ ተቃዋሚዎችን በማሰባሰብና መድረክ በመስጠት፣ ቆየት ብሎ ሶማሊያ ውስጥ ያለውን አልሸባብን በማንቀሳቀስ፣... ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የግብፅና የሳዑዲ ዓረቢያ መንግስታት በፍቅር ክንፍ ማለታቸው ይስተዋላል። ግብፃዊ ሹማምንት ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ ገባ ወጣ ማለት አብዝተዋል። በሁለቱ ሀገሮች መካከል ያለው ዲፕሎማሲዊ ግንኙነት በመጠናከሩ ለ50 ዓመታት በግብፅ እጅ የነበረች ደሴትን ለሳዑዲ ዓረቢያ እስከ መስጠት ተደርሷል። አዲሲቷ ደሴት ደግሞ ለሳዑዲ ንጉሳውያን ቤተሰቦች ተጨማሪ የመዝናኛ መንደር ለመመስረት ታስፈልግ ይሆናል።

ግብፅም ብትሆን ያልተረጋጋ ህዝቧ ጋር እየተነታረከች ደሴትን ያህል ነገር "በብላሽ ትሰጣለች" ብሎ ማሰብ፤ ማሰብ አለመቻል ነው። የሳዑዲ ዓረቢያ መንግስት ደሴት ካገኘ በኋላ ግብፅ "አድርግ" ያለቺውን "አያደርግም" ብሎ ማሰብም፤ ማስተንተን አለመቻል ነው እንጂ ሌላ ሊባል አይቻልም።

ለህዳሴ ግድብ ግንባታ የሚሆን ገንዘብ ማሰባሰብ እንደተጀመረ ሼህ ሙሐመድ 1.5 ቢሊየን ዶላር የሚያወጣ ድጋፍ ማድረጋቸው ይታወሳል። እዚህ ላይ መታየት ያለበት ሼህ ሙሐመድ ያበረከቱትን 1.5 ቢሊየን ዶላር ብቻ ሳይሆን፤ የእርሳቸውን አርአያነት ተከትለው ሌሎች የሀገሪቱ ባለሀብቶች ያደረጉት መጠነ ሰፊ ተሳትፎ ያስገኘውን ውጤት ነው። እንዲህ ያለው የኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች የትብብር መንፈስ ደግሞ በግብፆች ዘንድ በስጋት የሚታይ "መጥፎ ተግባር" ነው። እናም እንዲህ ያለውን ሁኔታ በተገኘው አጋጣሚ እንዲቋረጥ ለማድረግ "ይህንን ሰው አስደንግጡልን" የሚል መልእክት ከግብፅ ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ "አይተላለፍም" ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው።

**ሦስተኛው ነጥብ፤** ሳዑዲ ዓረቢያ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የተደረገ ዳሰሳ ነው። ከርቀት ስናየው በዚህ ወቅት በሳዑዲ ዓረቢያ ያለው "አልጋ" የረጋ አይመስልም። ወጣቱ ልዑል የለውጥ ኃይል (ሪፎርሚስት) ናቸው ይባላል። አዘማኝ (ሞደርኒስት) ናቸውም እየተባለ ነው። በቅርቡ ካከናወኗቸው አውሮፓ አስተኔ ተግባራት ውስጥ ሴቶች መኪና እንዲነዱ ፈቅደዋል። የመናፍስት ቀን (Halloween Day) በሳዑዲ ዓረቢያ እንዲከበር ፈቅደዋል። ለአንድ ሮቦት ዜግነት ሰጥተዋል... እንዲህ ያለው ተግባራቸው ግን በሳዑዲ ዓረቢያ "ኅምቱዎች" የተወደደላቸው እንዳልሆነና ውስጥ ውስጡን "የመፈንቅለ ስልጣን" ሴራ እየተውጠነጠነ እንደነበርም ይወራል። ተጽእኖ ፈጣሪና ተሰሚነት ካላቸው የሳዑዲ ዓረቢያ "ኅምቱዎች" ውስጥ ደግሞ ሼህ ሙሐመድ አንዱ መሆናቸውን ታሳቢ ማድረግ ይቻላል። እናም የአሁኑ የመንግስት እርምጃ ጠንካራ የፖለቲካ ክንድን ተጠቅሞ እነዚህን "ኅምቱዎች" ዝም ለማስባል የተለቀቀ "shock therapy" ይመስላል።

ከዚህ በተጨማሪ ከሼህ ሙሐመድ ጋር የተያያዘ ሌላ ዓቢይ ጉዳይ ማንሳት ይቻላል። ይኸውም የሳዑዲ መንግስት በቀይ ባህር ዳርቻ ከጂዳ ከተማ ትንሽ ራቅ ብሎ "አብደላ" የተባለ አዲስ ከተማ (Abdela

City) ለመቆርቆር አስቧል ይባላል። ይህም ከተማ ለሳውዲ ዓረቢያ ዜጎች የተከለከለ (የሳውዲ ዜጎች የማይገቡበት)፣ የውጪ ሀገር ዜጎች ብቻ የሚኖሩበትና እንደልባቸው የሚሆኑበት፣ መጠጥም ጭፈራም... የተፈቀደበት ከተማ እንደሚሆን ይወራል።

በአሜሪካ በኩል፤ ይህንን ከተማ የአሜሪካ (የእነ ትራምፕ) የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች እንዲሰሩት ይፈለጋል። በሳውዲ ዓረቢያ በኮንስትራክሽን ሥራ ታዋቂ የሆኑት የቢላደን ቤተሰብ እና የእነ ሼህ ሙሐመድ ድርጅቶችም "አገር በቀሎቹ እኛ እያለን የውጪ ሀገር ኩባንያ ሊመጣ አይገባም" የሚል አቋም መያዛቸውና ንትርክ መነሳቱ ይነገራል።

በሌላ በኩል የሳውዲ ዓረቢያ መንግስት ይህንን ከተማ ለመገንባት በቂ በጀት የሌለው በመሆኑ ቁንጮ ቱጃሮቹ ገንዘብ እንዲሰጡት ካለበለዚያ ትልቁን የነዳጅ ሀብት ድርሻ (ሼር) ለህዝብ እንደሚሸጥ ያስጠነቅቃል። ከወደ ቱጃሮ በኩል ደግሞ፤ "የነዳጅ ሀብት ድርሻችን ተቀንሶ ለህዝብ አይሸጥም። ለከተማው መገንቢያ ገንዘብ እንሰጣለን። ገንዘቡን የምንሰጠው ግን የግንባታ ስራው ለእኛ ከተሰጠን ነው..." የሚል ወጣሪ ቅድመ-ሁኔታ ሲነሳ፤ የሳውዲ መንግስት በበኩሉ "እምቢ ካላችሁ በሙስና ሰበብ እናንተን አስሬ ሀብታችሁን እወርሳለሁ..." የሚል አቅጣጫን በመከተል ነው ዋና ዋናዎቹን ሰዎች ያገተው እየተባለ በአረብ ሀገራት በስፋት እየተወራ ነው።

ለእነ ሼህ ሙሐመድ መታሰር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎችንም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መላምቶችን (Hypothesis) መዘርዘር ይቻላል። ይሁን እንጂ፤ የፈለግነውን ያህል መላምት ስንደረድር ብንውል እነ ሼህ ሙሐመድ የታሰሩበትን ምክንያት እቅጩን መናገር አይቻልም። እውነቱን የሚያውቀው አንድዬ የሆነው ፈጣሪ አምላክ - አላህ ብቻ ነው።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በደፈናው እነዚህን ሰዎች ያሳሰራቸው ከጀርባቸው እየተውጠነጠነ የነበረ ፖለቲካዊ ሴራ (Political Framing) ሊሆን እንደሚችል መጠርጠር ይቻላል። ፖለቲካዊ ሴራ (Political Framing) ማለት "አንድን ንፁህ ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ማህበረሰብ... ባልዋለበትና ባልሰራው ኃጢያት አቅዶና ሆን ብሎ፣ ሴራ በመጎንጎንና ሰነዶችን በማቀነባበር በህዝብና በፍትህ አካላት ተጠያቂ ለማድረግ የሚሸረብ ፖለቲካዊ ሴራ" ማለት ነው ይላሉ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ተንታኞች።

እንዲህ ያለው የሴራ ፖለቲካ አሜሪካንን ጨምሮ በአውሮፓና በሌሎችም በርካታ ሀገሮች ይፈጸማል። በእኛም በገር (የሩቁን ዘመን ትተን) ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የስልጣን ተቀናቃኞችን፣ አልታዘዝም ባዩን፣ አፈንጋጭን፣... ለማንበርከክ መንግስታት የሚጠቀሙበት የሸርና የተንኮል መንገድ ነው። (ወንድማችንን ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲንን ከእንዲህ ያለው ሸፍጥ አላህ ይጠብቃቸው!!!)

ሳር ቤት አካባቢ ወደሚገኘው የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ (መቻሬ ሜዳ) በሄድኩ ቁጥር ከሼህ ሙሐመድ ትልቅ ፎቶግራፍ ስር የተጻፈ ሁሌም ቀልቤን የሚስብ አንድ ጥቅስ አለ። እንዲህ ይላል፤ "ፈረሱም ሜዳውም እነሆ። አንድና አንድን በማቀናጀት አስር ለማድረግ በርትታችሁ ስሩ" ይላል። ይህ ጥቅስ ከሼህ ሙሐመድ ንግግር ላይ የተወሰደ ነው። መቼና የት እንደተናገሩት ባላውቅም ሼህ ሙሐመድ ይህንን "ሚሽን" (ተልእኮ) የሰጡት በኩባንያዎቻቸው ለሚሰሩ ሰራተኞቻቸው መሆኑ ነው።

መጀመሪያ ላይ አንድ እና አንድ ተቀናጅቶ እንዴት አስር ሊሆን እንደሚችል አልገባኝም ነበር። በኩባንያዎቹ ያለውን ስራና የአሰራር ስርዓት እንዲሁም በየዓመቱ የሚመዘገበውን ውጤት ሳይ ይህ ሼህ ሙሐመድ ለሰራተኞቻቸው የሰጡት ሚሽን ግልጽ ሆኖልኛል።

"ድንጋይና ቅዝምዝም የሚወረወረው ጣፋጭ ፍሬ ያፈራ ዛፍ ላይ ነው" እንዲሉ ሼህ ሙሐመድ የታሰሩት ታላቅ የስራ ሰው በመሆናቸው ነው እንጂ በነውረኛ ነገር ውስጥ ተገኝተው እንዳልሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ስራቸው ህያው ምስክር ነው። እንዲህ ያለው ውንጀላም ሆነ የሊቀ መንበራችን መታሰርና መንገላታት

አያስበረግገንም! እርሳቸው ታሰሩም ተፈቱ፣ በሀገር ውስጥ ኖሩም አልኖሩ… እርሳቸው የሰጡንን አንድ እና አንድን በማቀናጀት አስር የማድረግ ተልእኮ ለማሳካት መላው ሰራተኛ በበለጠ ትጋትና ጥንካሬ የምንሰራ መሆኑን ወዳጅም ጠላትም ሊያውቀው ይገባል።

በመጨረሻም፤ የሳዑዲ ዓረቢያን የሙስና ዘመቻ በተመለከተ አንዲት ነገር ለማንሳት ወደድሁ። በቅርቡ የሳዑዲ ንጉሳዊ ቤተሰቦች ወደ ፈረንሣይ ፓሪስ ለመዝናናት ሄደው ነበር። መሄዳቸው የሚገርም ነገር አይደለም። የሚገርመው ነገር ከንጉሳዊ ቤተሰቡ ጋር ከሳዑዲ ዓረቢያ ወደ ፈረንሳይ ተጭኖ የሄደው “ጓዝ” ብዛት ነው። ክብደቱ 25 ቶን (2,500 ኩንታል) ነበር። ይህንን “ጓዝ” ከአውሮፕላን ማረፊያ ወደ አረፉበት ሆቴል ለማጓጓዝ፣ ለመጫኛና ለማውረድ የነበረውን ውጣ ውረድ አስቡት። ሆቴሉ ውስጥ ወደ ፎቅ ለማውጣት የሆቴሉ አሳንሳር አልችል ብሎ እንደነበርም ዘገባዎች ያመለክታሉ።

ለመሆኑ ይህ ሁሉ “ጓዝ” ምንድነው? ልብስ ከሆነ አንድ ሁለት ሻንጣ ይበቃል። ቤትና አገር የለቀቁ ይመስል ዐረቢ መጅሊስ፣ መኪናና ምግብ ጭምር ጭኖ ሽርሽር ከመሄድ በላይ ብክነትና ሙስና አለ? የሳዑዲ መንግስት ሙስናን እዋጋለሁ ማለቱ ከልቡ ከሆነ መጀመሪያ በንጉሳዊ ቤተሰብ የሚፈጸመውን ልቅ ኑሮና መረን የለሽ ብክነት እንዲቀር ማድረግ ቢጀምር መልካም ነው። በርግጥ ሙስናን ከልብ እንዋጋ ካሉና ዘመቻውንም ከቤት ከጀመሩ የንጉሳዊ ቤተሰቡ መኖሪያ ከርቸሌ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ይህንን ሳያደርጉ በሌሎች ላይ ጣት መቀሰሩ ግን የአንድ ሰሞን ሆይ ሆይታን ከመፍጠር የዘለለ ትርጉም አይኖረውም።

ሼህ ሙሐመድ መታሰራቸው እንደተሰማ “የድርጅቱ ባለቤት የሉም፣ ታስረዋል፣ አይመጡም…” በሚል አስተሳሰብ አንዳንድ ወገኖች በአንዳንድ ኩባንያዎች ላይ ያሳዩትን አሉታዊ እንቅስቃሴ በተመለከተ እና ከሼህ ሙሐመድ መታገት ጋር የተያያዙ ተጨማሪ ሃሳቦችን ይዤ እመለስበታለሁ። እስከዚያው ድረስ ሊቀ መንበራችን እንደሚፈቱም ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ - ኢንሻ-አላህ!!!